# ከክልል መንግሥታትና ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የቅድመ-ታክስ ክፍያና ሌሎች የጋራ ገቢዎች ስለሚተላለፉበት አሠራር የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ነሐሴ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ከክልል መንግሥታትና ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ቅድመ ታክስ ክፍያ እና ሌሎች የጋራ ገቢዎች ስለሚተላለፉበት አሠራር

## መመሪያ ቁጥር 22/2001

ከክልል መንግስታትና ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች የሚሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ የክልልና የከተማ አስተዳደሮች ገቢ በመሆኑ በወጪ አሸፋፈናቸው ላይ ተጽእኖ በማያስከትል ሁኔታ በወቅቱ መተላለፍ ስለሚኖርበት፣

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 52 እና አንቀጽ 53 አማካይነት በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገው ከተከፋይ ሂሣቦች ላይ በቅድሚያ ተቀናሽ የሚደረገው የቅድመ-ታክስ ክፍያ ገቢ ባለቤት ለሆኑት ገቢ ሰብሳቢ አካላት የሚተላለፍበትን ሥርዓት በወጥነት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የፌዴራል መንግሥትና የክልል መንግሥታት የጋራ ገቢዎች ስለሚከፋፈሉበት ቀመር ላስተላለፈው መመሪያ ተግባራዊነት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተሰጠውን ውክልና ተፈፃሚ በማድረግ የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች ከጋራ ገቢ ድርሻቸውን በወቅቱ እንዲያገኙ ለማስቻል፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በየሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 27 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች የሚሰበሰብ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የቅድመ-ታክስ ክፍያና ሌሎች የጋራ ገቢዎች ስለሚተላለፉበት አሠራር የወጣ መመሪያ ቁጥር 22/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. "የሚተላለፍ የተጨማሪ እሴት ታክስ" ማለት በባለሥልጣኑ አማካይነት ከክልል መንግሥታትና ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋዮች ተሰብስቦ እንደየድርሻቸው ለነዚሁ አካላት የሚተላለፈው የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡
2. "የቅድመ-ታክስ ክፍያ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 52 እና አንቀጽ 53 ድንጋጌዎች መሠረት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለው እና ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ቀሪ የሚደረገው የገቢ ግብር ነው፡፡
3. "የጋራ ገቢ" ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 98 የተመለከተው እና በፌዴሬሽን ምክር ቤት በተዘጋጀ ቀመር መሠረት በፌዴራል መንግሥትና በክልል ወይም ከተማ አስተዳደሮች መካከል የሚከፋፈል የጋራ ገቢ ነው፡፡
4. "የግብር ሰብሳቢ አካላት" ማለት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ወይም የከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው፡፡
5. "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሠረት የሚሰበሰበውን ታክስ፣ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን፣ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ቀሪ የሚደረገውን ቅድመ ታክስ ክፍያ፣ የጋራ ገቢ፣ የሮያሊቲ ክፍያና በማዕድን ገቢ ግብርና ፔትሮሊየም አዋጅ መሠረት የሚጣለውን ግብር በተመለከተ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. በባለሥልጣኑ ተሰብስበው ለክልል መንግስታትና ከተማ አስተዳደሮች ገቢ ሰብሳቢ አካላት ስለሚተላለፉ ገቢዎች

1. የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ-ታክስ ክፍያን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

   ሀ. የሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ-ታክስ ክፍያ ከፌዴራል ወይም ከክልልና ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋይ መሆኑን በመለየት ገቢውን በአደራ የሂሣብ ኮደ /5426/ ይመዘግባል፣

   ለ. ከክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ግብር ከፋይ ለሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ-ታክስ ክፍያ ለግብር ከፋዩ ደረሰኝ ይሰጣል፣

   ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ለተላለፈው ገንዘብ የግብር ከፋዩን ሥም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፤ አድራሻና የገንዘብ መጠን እንደዚሁም የተከፈለውን የባንክ ኮሚሽን አገልግሎት በማካተትና ዝርዝር ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ገቢ ሰብሳቢ አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፣

   መ. ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን 3% /ሦስት በመቶ/ ቅድመ-ታክስ ክፍያ የፌዴራል መንግሥት ድርሻ የሆነውን በገቢ ኮድ ቁጥር 1104፣ የክልልና ከተማ መስተዳድሮችን ደግሞ በአደራ የገቢ ኮድ ቁጥር 5026 ይመዘግባል፣ የእያንዳንዱን ግብር ከፋይ ሥም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የግብር ክፍያ መጠን በመለየትም መረጃውን ለሚመለከታቸው የክልልና ከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ አካላት፣ ገቢውን ጨምሮ ወሩ ባለቀ በ30 ቀናት ውስጥ ያስተላልፋል፣

   ሠ. እያንዳንዱ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሰበሰበውን ገቢ ወሩ ባለቀ ከ10 /አሥር/ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ ባለሥልጣኑ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሣብ/አካውንት ያስተላልፋል፣ በተጨማሪም የታክስ ከፋዩን ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ክልል/ከተማ አስተዳደር እንደዚሁም ለባንክ አገልግሎት የተከፈለውን ወጪ በመለየት ለገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሣቦች ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ. የባለሥልጣኑ የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሣቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአደራ ሂሣብ ገቢ የተደረገውን የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅድመ-ታክስ ክፍያ ገቢው የተሰበሰበበት ወር እንዳበቃ ቀጥሎ ባሉት 30 /ሰላሳ/ የሥራ ቀናት ውስጥ የገቢው ባለቤት የሆነው የክልል መንግሥት ወይም የከተማ አስተደደር ባስታወቀው ወይም በሚያስታውቀው የባንክ ሂሣብ ገቢ ያደርጋል፣

ሰ. የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶችና በአዲስ አበባ የሚገኙ የቅድመ-ታክስ ክፍያ ሰብሳቢ አካላት ማለትም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው የግል ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ታክሱን ከሰበሰቡ በኂላ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልተው ለባለሥልጣኑ ከነቅጹ ገቢ ያደርጋሉ፣

ሸ. የክልል ባለበጀት መሥሪያ ቤቶችና በየክልሉና ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ቅድመ-ታክስ ክፍያ ሰብሳቢ አካላት ታክሱን ከሰበሰቡ በኂላ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለክልሉ/ከተማ አስተዳደር የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ገቢ ያደርጋሉ፣

ቀ. ግብር ከፋዮች ግብሩን ቀንሰው እንዲያስቀሩ በህግ ሥልጣን ከተሰጣቸው ወገኖች በተሰጣቸው ደረሰኞች መሠረት በየዓመቱ መጨረሻ ከሚከፍሉት ወይም ከሚወሰንባቸው ግብር/ታክስ ላይ ይካካስላቸዋል፣

በ. እያንዳንዱ ግብር ከፋይ የቅድመ-ታክስ ክፍያ ግብር የፈጸመበትን ደረሰኝ የግብር መክፈያ ማህደሩ ላለበት የግብር ሰብሳቢ አካል አቅርቦ ተገቢውን አገልግሎት ሲጠይቅ፣ የግብር ሰብሳቢው አካል ገንዘቡ ቢተላለፍለትም ባይተላለፍለትም ግብር ከፋዩ ያቀረበውን ደረሰኝ ትክክለኛነት በማረጋገጥና ፎቶ ኮፒውን ከዋናው ጋር አመሳክሮ በማስቀረት ሂሳቡ በታሳቢ እንደተከፈለ በመቁጠር ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፣

ተ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(7) የተመለከተው ቢኖርም የደረሰኙ ትክክለኛነት አጠራጣሪ በሚሆንበት ወቅት ዋናውን ደረሰኝ ጭምር በመያዝ ለተጨማሪ ማጣራት አግባብነት ላለው የሥራ ሂደት ፈጥኖ ያስተላልፋል፣

2. በባለሥልጣኑ በኩል የሚሰበሰበውን የጋራ ገቢን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

   ሀ. በጋራ ከተቋቋሙ የልማት ድርጅቶች፣ ከግል ድርጅቶችና ከከፍተኛ የማዕድንና የፔትሮሊየም ሥራዎች የሚሰበሰበውን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የተርንኦቨር ታክስ፣ የኤክሳይዝ ታክስ፣ የባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ /ዲቪደንድ/ እና የሮያሊቲ ገቢ ግብር/ታክስ በአደራ የገቢ ሂሣብ መደብ 5426 በመመዝገብ ለዚሁ በተከፈተው የባንክ አካውንት/ሂሳብ ገቢ ያደረጋል፣

   ለ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) “ሀ” ከተመለከቱት ታክሶች የሰበሰበውን የጋራ ገቢ የተሰበሰበበትን ድርጅት ሥም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ አድራሻና የገንዘቡን መጠን በየገቢው ዓይነትና ኮድ በመለየት ዝርዝር መረጃ ያጠናቅራል፣

   ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) ፊደል “ለ” የተመለከተውን ዝርዝር መረጃ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚተላለፈው የጋራ ገቢዎች ክፍፍል ጥምርታ /በሥራ ላይ ያለው በአባሪነት ተያይዟል/ መሠረት በክልል መንግሥታት፣ በከተማ አስተዳደሮችና በፌዴራል መንግሥት መካከል ያከፋፍላል፣

3. የተሰበሰበ የጋራ ገቢ የሚተላለፍበትን ጊዜ በተመለከተ

   ባለሥልጣኑ የሰበሰበውን ገቢ በሚከተለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ለክልል መንግሥታትና ከተማ አስተዳደሮች ያስተላልፋል፡፡

   ሀ. የንግድ ትርፍ ግብር፣ የባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ /ዲቪደንድ/ እና የሮያሊቲ ክፍያዎች/ገቢዎች የበጀት ዓመቱ አልቆ ከጥቅምት 30 በኂላ ባሉት የሶስት ወር ጊዜ ውስጥ፣

   ለ. ሂሣባቸውን በአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ታህሳስ መጨረሻ ላይ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ የሂሣብ ጊዜ ለሚዘጉ ከሚያዝያ መጨረሻ ጀምሮ ከተፈቀደው ወይም የሂሣብ መዝጊያ ወር መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 3/ሶስት/ ወራት ጊዜ ውስጥ፣

   ሐ. የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የተርንኦቨር ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ የክፍያ ወሩ ባለቀ በሚቀጥሉት 30 ቀናት ውስጥ፣

5. <u>የቼክ መመንዘሪያ አካውንት ስለመክፈት</u>

ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱት ገቢዎች ክፍያ የተፈጸመው በቼክ ከሆነ ለቼኮቹ መመንዘሪያ የሚያገለግል የአደራ የባንክ ሂሳብ ይከፈታል፣ ይህም የባንክ ሂሣብ በየዓመቱ መጨረሻ የማይዘጋ (Block የማይደረግ) ይሆናል፡፡

6. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄን ለማስተናገድ ተቀናሽ ስለሚደረግ ሂሣብ</u>

1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የሚጠይቁ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋዮችን ማስተናገድ እንዲቻል ከክልሎችና ከፌዴራል መንግሥት ግብር ከፋዮች ላይ ከተሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ላይ 10% /ከመቶ አስር/ ተቀንሶ ለዚሁ ሂሣብ ማስተዳደሪያ በሚከፈት የባንክ ሂሣብ ገቢ ይደረጋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው ሂሣብ ላይ ባለው አሠራር መሠረት ተገቢው ማጣራት ተደርጐ የተመላሽ ጥያቄው ይስተናገዳል፡፡
3. አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻልም ስለተመላሽ ሂሣብ በየስድስት ወሩ ሪፖርት ይዘጋጃል፣ ስለአጠቃላይ አፈጻጸሙም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ይቀርባል፣

7. በክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ግብር ሰብሳቢ አካላት የሚሰበሰቡ የፌዴራልም ሆነ የጋራ ገቢዎች ለባለሥልጣኑ ስለሚተላለፉበት ሁኔታ በሚሰጥ ውክልና ወይም በጋራ መግባቢያ ሰነድ ላይ ይወሰናል፡፡

8. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የነበሩ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተክተዋል፡፡

9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ__________ ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር